ጥቅምት 18 ቀን 2000ዓ.ም

# ማስታወቂያ

**ጉዳዩ፡-** ሀገራቸው ውስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ባንክ ሂሣብ መክፈት

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በትውልድ ሀገራቸው ውስጥ በሚገኙ ባንኮች በውጭ ምንዛሪ ባንክ ሂሣብ መክፈት እንዲችሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት አመልካቾች በአካል ቀርበው በኢትዮጵያ ንግድ ባንኮች የውጭ ባንክ አካውንት እንዲከፍቱ፡ ሲደረግ የቆየ መሆኑ ይታወሳል፡፡

ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንኮች በተጨማሪ በአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ በአቢሲኒያ ባንክ በቅርንጫፍ ባንኮቻቸው የውጭ ምንዛሪ የባንክ አካውንት መክፈት የሚቻል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከላይ በተጠቀሱት በሁሉም ባንኮች በግልም ሆነ በጋራ አካውንት ለመክፈት የሚሞሉ ፎርሞች በኤምባሲያችን የሚገኙ በመሆናቸው ቀደም ሲል ጥያቄ አቅርባችሁ የነበራችሁም ሆነ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን የምትፈልጉ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ቤት መሄድ ሳያስፈልግ ወደ ኤምባሲያችን በመምጣት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

*የኢትዮጵያ ኤምባሲ*

*ስቶክሆልም*

ነሀሴ 28 ቀን 2000ዓ.ም

**ማስታወቂያ**

**ጉዳዩ፡-** ማስታወቂያ ለአክሲዎን ፈላጊዎች

Sky Bus Transport System Share Company በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በትራንስፖርት ዘርፍ አክሲዮን ገዝተው ለሀገራቸው ብሎም ለራሳቸው አስተዋፅዎ እንዲያደርጉ ይጋብዛዋል፡፡

በመሆኑም ፍላጉቱ ያላችሁ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከማህበሩ አክሲዮን በመግዛት በዘርፉ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

*የኢትዮጵያ ኤምባሲ*

*ስቶክሆልም*

**የማህበሩ ዓላማ** መንግስት ፈጣንና ዘላቂ ልማት ለማስመዝገብ ሃገራችንን ከድህነት ለማላቀቅና ድህነትን ታሪክ ለማድረግ በቁርጠኝነት በሚንቀሳቀስበት በአሁኑ ወቅት በሐገር አቋራጭ የሕዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት በኩል የጎላ ችግር ይስተዋላል፡፡

**የማህበሩ ራዕይ** ልክ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ በምድር ትራንስፖርት ዘርፍ የፕሮፌሽናል ደረጃን የጠበቀ ግዙፍና ገናና ኢትዮጵያዊ የትራንስፖርት ኩባንያ መገንባት ነው፡፡

አራት ሺህ (4000) አባላትን በማስተባበር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በምዝገባ ቁጥር 020/2/5046/2000 የተመዘገበ አክሲዮን ማህበር ነው፡፡

ድርጅታችን በዓለምአቀፍ ያሉ የኢትዮጵያ ዜጎች የስካይ ባስ ትራንስፖርት ሲስተም አክሲዮን ማህበር አባል በመሆን ራሳቸውን ብሎም ሃገራቸውን ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ መሆኑን ስንገልጽላቸው በታላቅ አክብሮት ነው፡፡

የስካይ ባስ ትራንስፖርት ሲስተም አክሲዮን ማህበር አክሲዮን ግዢ የሚፈፀመው በባንክ አማካኝነት በስካይ ባስ ትራንስፖርት ሲስተም አክሲዮን ማህበር ዝግ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ በማስገባት የአክሲዮን አባል መሆን ይቻላል፡፡

የአገልግሎት ክፍያ ደግሞ በግሪን ሆርስ ማኔጅመንት እና ማርኬቲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ. ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ቁጥር በማስገባት ይሆናል።

ግሪን ሆርስ ማኔጅመንት እና ማርኬቲንግ ኃ.የተ.የግ.ማ. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስትር በምዝገባ ቁጥር 020/2/4966/2000 የተመዘገበ የንግድ ማህበር ነው።

ይህም ኩባንያ የሃገር ውስጥ ድርጅት ሲሆን በዋናነት የተሰማራው በሃገራችን ውስጥ ያሉትን የንግድ ዘርፍ ክፍተቶችን በማጥናት፣ በፈጠራ የሚገኙ መፍትሄዎችን በማሳደግ ከዚያም ተግባራዊነታቸውን በመከታተል ለውጤት የሚያደርስ የግል ድርጅት ሲሆን የመጀመሪያውም ኩባንያ ስካይ ባስ ትራንስፖርት ሲስተም አክሲዮን ማህበር ሲሆን በቀጣይም ለሃገራችን የሚጠቅሙና አትራፊ የሚሆኑትን ፕሮጀክቶች በማቋቋም ላይ ያለ ድርጅት ነው።

## ለበለጠ መረጃ፡

ስልክ ቁጥር፡+251 116 180160/+251 911 44 2657/+251 911 102407
+251 911 671634/+251 911 643112
ፋክስ ቁጥር፡ +251 116 180941
ድረ-ገጽ፡ www.SkyBusEthiopia.com
ኢ-ሜል: Solomon@SkyBusEthiopia.com
Abiy@SkyBusEthiopia.com
Milkias@SkyBusEthiopia.com

ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም.

## ማስታወቂያ

**ጉዳዩ፡ - በግል የመኖሪያ ቤት የቦታ ጥያቄ አመልካቾች**

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግልና በማህበር በመደራጀት የመኖሪያ ቤት ለመስራት እንዲችሉ ባወጣው የቦታ አሰጣጥ መመሪያ መሠረት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በስፋት እያስተናገደ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

በክልሉ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ዙሪያ እስከ 100 ማይልስ ድረስ በሚገኙ ከተሞች ለመኖሪያ ቤት የተዘጋጀ ቦታ በመጠናቀቁ እነዚህን ከተሞች በሚመለከት የሚቀርቡ የቦታ ጥያቄዎችን ማስተናገድ መቆሙን የክልሉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም. ለኤምባሲያችን በጻፈው ደብዳቤ በመግለጽ ይኸው ለማህበረሰቡ እንዲተላለፍ ጠይቋል፡፡

ስለሆነም በኦሮሚያ ክልል በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያ እስከ 100 ማይልስ ድረስ ባሉት ከተሞች ለመኖሪያ ቤት የተዘጋጀ ቦታ የተጠናቀቀና ለጊዜው የተዘጋጀ የሌለ መሆኑ ታውቆ የቦታ ዝግጅት እስኪደረግ ድረስ የሚቀርቡ የቦታ ጥያቄዎችን ከ100 ማይልስ ክልል ውጭ ባለው ክልል ውስጥ የሚስተናገዱ መሆኑን እናስተውቃለን፡፡

*የኢትዮጵያ ኤምባሲ*

*ስቶክሆልም*

ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም.

## ማስታወቂያ

**ጉዳዩ ፡- የትምህርት ማስረጃዎችን ስለማረጋገጥ**

በውጭ ሀገር ለተገኙ የትምህርት ማስረጃዎች አቻ ግምት ለመስጠት ማስረጃዎቹ በተገኙበት ሀገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ መምጣት ያለበት ቢሆንም በውጭ ሀገር ተምረው የሚመለሱ ተማሪዎችና የአገልግሎቱ ጠያቂዎች ይህን ባለመገንዘብ የትምህርት ማስረጃቸው አቻ ግምት እንዲሰጣቸው እየጠየቁ በመሆኑ ሕጋዊ ያልሆኑ ዶክመንቶችን ለመለየትና አገልግሎቱን በተገቢው መንገድ ለመስጠት ችግር እየፈጠረ ይገኛል፡፡

ስለሆነም በውጭ ሀገር ትምህርታችሁን በመከታተል ላይ የምትገኙ ዜጐች ትምህርታችሁን አጠናቃችሁ ስትመለሱ በተማራችሁበት ሀገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የትምህርት መረጃዎቻችሁን ትክክለኛነት እንድታረጋግጡ የትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ ያስተላለፈ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

የኢትዮጵያ ኤምባሲ
ስቶክሆልም